---------- ኃ/የተ/የግ/ማህበር

የመተዳደሪያ ደንብ

አንቀጽ 1

ጠቅላላ ድንጋጌ

1.1 ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ጋር በአንድነት የማይነጣጠል አካል ሆኖ ያገለግላል።

1.2 ማህበሩ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንቀጽ 510 እስከ 543 በተመለከቱተት ድንጋጌዎች የተቋቋመና በዚሁ መተዳደሪያ ደንብ እና ተያይዞ በሚገኘው የመመስረቻ ጽሁፍ የሚገዛና የሚተዳደር ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነው። ስለሆነም በመተዳደሪያ ደንቡና በመመስረቻ ጽሁፉ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በኢትዮጵያ ንገድ ህግ ውስጥ ስላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 2

ካፒታል

2.1 የማህበሩ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ ብር ----------/----------/ በሙሉ የተከፈለ ጠቅላላ ብር----------/----------/ ነው።

2.2 ከማህበሩ አባላት ቢያንስ የካፒታሉን 3/4 ኛ ድርሻ የያዙት አባላት ሲስማሙ የማህበሩን ካፒታል አንድ ጊዜ ወይም ብዙ ጊዜ ማሳደግ ይቻላል። በዚህ ጊዜ አክሲዮኖቹ በተጨማሪነት የሚመደቡት ባለአክሲኖች ቀደም ሲል በነበራቸው የአክሲዮን መጠን ልክ ይሆናል። የካፒታል ጭማሪ የኢትዮጵያ ንግድ በሚፈቅደው በማንኛውም መንገድ ሊሆን ይችላል።

አንቀጽ 3

አክሲዮኖች

3.1 አክሲዮኖች በማህበሩ አባላት መካከል ያለምንም ገደብ ሊተላፉ ይችላሉ። እንዲሁም የሚች አባል አክሲዮኖች ያለምንም ገደብ ወራሽነታቸውን ላረጋገጡ ወራሾች ይተላለፋሉ።

3.2 አክሲዮኖች ከማህበሩ ውጪ ላለ ሰው ማስተላለፍ የሚቻለው በቅድሚያ ቢያንስ ቢያንስ ከማህበሩ ካፒታል ሶስተት ሩብ(75%) የያዙትን አባላት ስምምነት ማግኘት ሲቻ ነው። የአባላቱ ስምምነት ካተገኘና አክሲዮን ማስተላለፍ የፈለገው አባል በሃሳቡ ከጸና ለሽያጭ የቀረበውን አክሲዮን የመግዛት ቅድሚያ የሚሰጠው ከአባላቱ መካከል ቀደምት ለሆነው ይሆናል። ከአንድ በላይ ቀደምትነት መብት ያላቸው ሰዎች አክሲዮን ለመግዛት ያላቸው ሰዎች አክሲን ለመግዛት ያላቸውን ቅድሚያ መብት ለመጠቀም የፈለጉ እንደሆነ ከመሃከለቻው በጨረታ አሸናፊ ለሚሆነው አባል ይሸጣል።

3.3 ከላይ በተገለጸው ሁኔታ የተደረገ የአክሲዮን ማስተላለፍ በጽሁፍ መሆን ያለበት ሲሆን በሰነድ አረጋገጭ ፊት ቀርቦ ካልተረጋገጠ እና ካልተመዘገበ ዋጋ አይኖረውም። የምዝገባ አስፈላጊነቱ አክሲዮን በሚመለከት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

አንቀጽ 4

ማህተም

ማህበሩ የራሱ የሆነ በማህበሩ ስም የተዘጋጀ ማህህተምና አርማ ይኖረዋል። ይህ ማህተምና አርማ ለማህበሩ ስራ አገልግሎት ብቻ ይውላል።

አንቀጽ 5

ስለማህበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች

5.1 እያንዳንዱ የማህበሩ አባል የሚከተሉት መብት ይኖረዋል

5.1.1 በማናቸውም የማህበሩ አባላት ስብሰባ ላይ መካፈል

5.1.2 በማናቸውም ስብሰባ ላይ በያዘው አክሲዮን ብዛት መጠን ድምጽ መስጠት

5.1.3 በዋናው መስሪያ ቤት ውስጥ የቆጠራ ውጤቶችን የወጪና ገቢ ምዝገባዎች እና የአዲት ሪፖርቶች የመመርመርና መዝግቦ የመያዝ

5.1.4 በህግ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተመለከቱትን መብቶች የመጠቀም

5.1.5 የሚች ማህበርተኞች ወራሾችም ሆኑ ወኪሎች በማህበሩ አባላቶች ንብረቶች ላይ ማህተም አንዲደረግ ወይም አንዲታሸግ ማድረግ መብት አይራቸውም። ስለሆነም በመብታቸው በሚጠቀሙበት ጊዜ ሁሉ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ የሚተላለፉ የማህበርተኞች ውሳኔዎች ሁሉ በነሱም ላይ ተፈጻሚነት አላቸው።

አንቀጽ 6

ያለስብሰባ የሚተላለፉ ውሳኔዎች

ጉባኤው አንዲሰበሰብ ህግ ወይም መተዳደሪያ ደንብ በሚያስገድድበት ጊዜ ዋና ስራአስኪያጅ ድምጥ ሊሰጥበት የተፈለገውን ጉዳይ ለእያንዳንዱ የማህበሩ አባላት በጽሁፍ በመላክ በጉዳዩ ላይ አባላት በጥሁፍ ድምጥ አንዲሠጡበት መጠየቅ አለበት።

አንቀጥጽ 7

ስብሰባዎች

7.1 የአክሲዮኑ የሂሳብ ዓመት ከተዘጋ ከ 4 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መጠራት አለበት ።

7.2 ዋናው ስራ አስኪያጅ ዓመታዊ የማህበርተኞች ስብሰባ ከመደረጉ በፊት 10 ቀን አስቀድሞ ለአባላቱ በአደራ ደብዳቤ የስብሰባውን ጥሪ ማሳወቅና ለውሳኔ ወይም ለውይይት የቀረበው ሀሳብ ምን እንደሆነ በግልጽ ማሰረዳት አለበት።

7.3 ኦዲተሩ ወይም በዋናው ገንዘብ ከግማሽ በላይ የሚወክሉ የማህበሩ አባላት በማናቸውም ጊዜ አክሲዮኑ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ሊደርጉ ይችላሉ።

አንቀጽ 8

ምልአተ ጉባኤ

8.1 የማህበሩ ስበሰባ ሊካሄድ የሚችለው ከዋናው አክሲዮን ½ ኛ በላይ ያላቸውን አባላት የሚወክሉ ማህበረተኞች ስብሰባ ለይ ሲገኙ ነው።

8.2 በዚህ ዓይነት ስብሰባዎች ላይ ውሳኔዎች የሚተላፉ በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

አንቀጥ 9

የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣን

9.1 የማህበሩን ዋና ስራ አስኪያጅ መግለጫ ሰምቶ ተቀባይነት ያው ሆኖ ካገኘው ያጸድቃል።

9.2 የማህበሩን ሂሳብ ተቆጣጣሪ (ኦዲተር) ዓመታዊ መግለጫ መርምሮ ተገቢውን እርምጃ የወስዳል።

9.3 የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ ይሾማል። በቂ ምክንያ ሲኖር በህግ አግባብ(በንግድ ህግ አንቀጽ 527(4)) መሰረት ይሽራል።

9.4 ለዋና ስራ አስኪያጅ ሊከፈል የሚገባውን አገልግሎት ዋጋ ይወስናል። በዚህ ስብሰባ ላይ ዋናው ስራ አስኪያጅ አባል ቢሆንም አይካፈልም።

9.5 የማህበሩን ስራ አፈጻጸም በሚመለከት ለዋና ው ስራ አስኪያጅ መመሪያ ይሰጣል።

9.6 ማህበሩን ማስቆጥት ወይም ማፍረስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ውሳኔ ይሰጣል።

9.7 ስለዓመታዊ ትርፍ አከፋፈል ውሳኔ ይሰጣል።

አንቀጽ **10**

የአክሲዮኑ በጀት የሂሳብ መግለጫና ህጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ

10.1 የማህበሩ የሂሳብ ዓመት እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከሀምሌ 1 ቀን ጅምሮ ዝስከ ሰኔ 30 ቀን ይፈጸማል። ስለሆነም የመጀመሪያው የሂሳብ ዓመት የመመስረቻው ጽሁፍና ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል።

10.2 በሂሳብ ዓመቱ የመጨረሻ የማህበሩን ንብረቶች እቃዎች የሚያሳይ ሚዛን (ባላንሥ) በዋና ስራአስኪያጁ ይዘጋጃል። ይህም ሚዛን እንደጸደቅና እንዲመረመር ለመኦዲተሮችና ለማበረተኞች ይተላፋል።

10.3 የማህበሩን ዓመታዊ ሁኔታ የሂሳብ ሚዛን የትርፍና የኪሳራ ሁኔታ የንብረት ቆጠራዎችና የዋና ስራ አስኪያጅ ወይም የኦዲተር ሪፖርት የሚሰዩ ሰነዶች በጊዜው ለአባላቱ ይላካሉ።

10.4 በነምግድ ህግ አንቀጽ 539 መሰረት በተጣራው የማህበሩ ገንዘብ ትርፍ ላይ በየዓመቱ መጠባበቅያ የሞህነውን ቢያንስአምስት በመቶ እየተነሳ ይቀመጣል። ይኼው መጠባበቂያ ከማህበሩ ዋና ገንዘብ አንድ አስረኛ እጅ ሲደርስ ግዴታ መሆኑ ይቋረጣል።

አንቀጽ **11**

የአዲተሮች ስልጣንና ተግባር

11.1 የማህበሩ ኦዲተሮች የማህበሩን የሂሳብ መዛግብት መመረመርና ከስራ አስኪያጅ አስፈላጊ ማብራርያ መጠየቅ ይችላሉ። እንዲሁም የማህበሩን የሂሳብ መዝገብና ሰነዶችን በመመርመር የሂሳብ ሪፖርት ላይ የማህበሩን የወደፊት እንቅስቃሴ ላይ አስፈላጊውን የገንዘብ ሂሳብ ያቀርባሉ።

11.2 የማህበሩን የሂሳብ መዛግብትና ዋስትና ሰነዶች ኦዲት ማድረግ።

11.3 የቆጠራ ሰነዶች የሂሳብ ሰነዶች ትርፍና ኪሳራ ማረጋገጥ።

11.4 ሪፖርቱ የማህበሩን ነባራዊ ሁኔታ በትክክል ማንጸባረቁን ማረጋገጥ።

11.5 ለጠቅላላ ጉባኤ ወይም በህግ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ሌሎች መሰል ሃላፊነቶችን ይወጣል።

አንቀጽ **12**

የዋና ስራ አስኪያጅ ክፍያዎች

ዋና ስራ አስኪያጅ ለአገልግሎቱ የሚከፈለውን እና የሚሾምብትን ሁኔታ በዝረዝር ማህበረተኞቹ ይወስናሉ።

አንቀጽ 13

የማህበሩ መፍረስ

13.1 ማህበሩ በንገድ ህግ አንቀጽ 217፣218፣511፣542፣እና 543 ላይ በተደነገገው መሰረት በቂ በሆነ ምክንያቶች ብቻ በፍ/ቤት ሊፈርስ ይችላል።

13.2 ከማህበሩ አባላት አንዱ ወገን የማህበሩን ቢጠይቅ ቀሪዎቹ ማበረተኞች ማህበሩ የሚያዋጣውን አክሲዮን ድርሻ በሂሳብ መዝገብ መሰረት ዋጋ በመ፣ክፈል የማህበሩን ስራ በመካከላቸው (በመተካት) ሊቀጥሉ ይችላሉ።

አንቀጽ 14

የመደምደሚያ ድንጋጌዎች ማስታወቅያ

14.1 የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ በግልጽ ያልተመለቱት ማናቸውም ጉዳዮች አግባ ባላቸው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ይታል፤፤

14.2 የማህበሩ አባላት ከላይ የተመለከተውን የመተዳደሪያ ደንብ አንብበንና ተረድተን ዛሬ ---------- 20..... ዓ.ም በየስማችን አንጻር በመፈረም ሰነዱን አጽድቀናል።

ተ/ቁ	የአባላት ስም	ፊርማ	መግለጫ

---------- ኃ/የተ/የግ/ማህበር

የመመስረቻ ጽሁፍ

እኛ ስማችን ዜግነታችን እና አድራሻዎቻችን በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸው ሰዎች በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 495 በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ የመመስረቻ ጽሁፉ አካል ሆኖ በሚቆጠረው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ..... ኃ/የተ/የግ/ማህበር(ከዚህ በኋላ ማህበሩ ተብሎ የሚጠራውን) መስርተናል።

አንቀጽ 1

የማህበሩ ስያሜ

ማህበሩ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተብሎ ይጠራል።

አንቀጽ 2

የመስራቾች ስም ዜግነትና አድራሻ

የመስራቾች ስም ዜግነት እና አድራሻቸው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ነው።

ተ/ቁ	ስም ከነአያት	ዜግነት	አድራሻ			
			ክልል	ክ/ከተማ/ዞን	ወረዳ/ቀበሌ	የቤት ቁጥር

አንቀጽ 3

የማህበሩ ዋና መ/ቤት

ሀ/ የማህበሩ ዋና መ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ .....ክ/ከተማ .....ወረዳ የቤት ቁጥር..... ነው።

ለ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማህበሩ በተለያዩ ክልሎችና ከተማዎች ቅርንጫፍና ወኪል መ/ቤቶችን ሊከፍት ይችላል።

አንቀጽ 4

የማህበሩ የንግድ ዓላማዎች

4.1 የግንባታ እቃዎችን ማስመጣትና ማከፋፈልና መቸርቸር

4.2 የግንባታ እቃዎች ማምረቻን በማቋቋም ማምረትና ለአገር ውስጥና ለውጪ አገር ገበያ ማቅረብ

4.3 ለግንባታ እቃዎችን ማምረቻ ፋብሪካዎች ጥሬ እቃዎችን ማቅረብ

4.4 ለተለያዩ ግንባታዎች የግንባታ እቃዎችን ማቅረብ

4.5 ትናንሽ ግንባታዎችን ማከናወን

4.6

4.7

4.8

4.9

4.10

አንቀጽ 5

የማህበሩ ካፒታል

1. የማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር
2. የማህበሩ የተከፈለ ካፒታል ብር
3. ያልተከፈለ የማህበሩ ካፒታል ብር
4. የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ ብር 1000.00(አንድ ሺህ ብር) ሲሆን የተፈረሙ የተከፈሉ እና ያልተከፈሉ አክሲዎኖች ድልድል ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል።

ተ/ቁ	ስም ከነአያት	የአክሲዮን ብዛት	የአንዱ ዋጋ	የተፈረመ	የተከፈለ	ያልተከፈለ	ጠቅላላ መዋጮ

አንቀጽ 6

የማህበሩ ትርፍና ኪሳራ አከፋፈል

6.1 የማህበሩ የበጀት ዓመት በየዓመቱ ከህምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ይሆናል። በዚሁ መሰረት መጀመሪያው የሂሳብ ዓመት የመመስረቻው ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንቡ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ድርስ ይሆናል ማለት ነው።

6.2 በእያንደንዱ በጀት ዓመት መጨረሻ የማህበሩን ንብረቶች እና እዳዎች የሚያሳዩ የፋናስ ሪፖርቶች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ይቀርባል።

6.3 በኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንቀጽ 458 መሰረት የትርፍ ድርሻዎች ለባለአክስዮኖች የሚከፈሉት እንደ አክሲዮን ድርሻቸው በደንብ ከጸደቀው የሂሳብ ሚዛን ውስጥ ከተገለጸው የተጣራ ትርፍ ነው። ዓመታዊ የጥርፍ ድርሻዎች አከፋፈል በባለአክሲኖች መደበኛ ጉባኤ ይወሰናል።

6.4 ከባለአክሲዮኖች መብታቸው በተጨማሪ መስራች ባለአክሲዮኖች ካላቸው አክሲዮን መጠን አንጻር ከጸደቀው የሂሳብ ሚዛን ውስጥ ከተገለጸው የተጣራ ትርፍ ላይ ከመቶ አምስት እጅ (5%) የማግኘት መብት አላቸው። ይህ መብት መማበሩ ትርፍ ማስመዝገብ ከጀ j መረበት ጊዜ ለሶስት ተከታተይ ዓመታት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

አንቀጽ 7

የማህበሩ አካላት

ማህበሩ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።

ሀ/የባለ አክሲዮን ጠቅላላ ጉባኤ

ለ/የዳይሬክተሮች ቦርድ

ሐ/ የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅና ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች

መ/ የውጪ አዲተሮች

አንቀጽ 8

የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

የባላ አክሲኖች ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ ከፍተኛ አካል ነው። በህግ በመመስራቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላላ ጉባኤ ዋና ዋና ስልጣንና ተግባራት የሚከተሉትን ይጨምራል።

1/ የማህበሩን ዳይሬክተሮች የመምረጥ ማሰናበት እንዲሁም ክፍያዎቻቸውን መወሰን

2/ የማህበሩን የውጪ ኦዲተሮች የመምረጥና ክፍያዎቻቸውን የመወሰን

3/ የትርፍና የኪሳራ መግለጫ የሀብት ሚዛን ማሳያ እና የዳይሬክተሮች ሪፖርት መገምገም

4/ የኦዲት ሪፖርት ማድመጥ

5/በትርፍ ክፍፍል ላይ ውሳኔ ማሳለፍ

አንቀጽ 9

የዳይሬክተሮች ቦርድ

9.1 ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይተዳደራል።

9.2 ማህበሩ በባለአክሲዮች ጠቅላላ ጉባኤ ሚመረጡ 5(አምስት) አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይኖሩታል። በዚህም መሰረት በመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡት የቦርድ አባላት ስም ዝርዝር እንደሚከተለው ነው።

1/

2/

3/

4/

5/

በተጨማሪም አቶ የቦርዱ ሊቀመንበር ሲሆን አቶ ደግሞ ም/ሊቀመንበር በመሆን ተመርጠዋል።

አንቀጽ 10

የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባራት

1. የዳይሬክሮች ቦርድ በህግ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በበላ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የተሰጧቸውን ስልጣንና ተግባራት የመወጣት ኃላፊነት አለባቸው።

2. በህግ በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል።

2.1 የማህበሩን ራእይ ተልእኮ እሰቶች ስትራቴጅክ ግቦችና እቅዶች በጀት ፖሊሲዎች መመሪያዎች እና ውስጠደንቦችን ማጽደቅ፡

2.2 የማህበሩን ዋና ስራ አስኪያጅ መቅጠር ደመወዙን የስራ አበሉን የመወሰን እና ከስራ የማሰናበት

2.3 ለዋና ስር አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የስራ ኃላፊዎችን ቅጥር ምደባና ስንብት ደመወዝ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ማጽደቅ

2.4 የማህበሩን ስራ አፈጻጸም መከታተል መቆጣጠርና መገምገም

2.5 የማህበሩን ብድሮች እና ክሬዲቶችን ማጽደቅ

2.6 የማህበሩን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ማጽደቅ

2.7 የማህበሩን ቅርንጫፍ መ/ቤቶች አከፋፈትና አዘጋግ ማጽደቅ

2.8 የማህበሩን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ማጽደቅ

2.9 የማህበሩን ካፒታል እንዲጨምር ለባለአክሲዮኖች ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ

2.10 የማበሩ ሂሳቦችና ንብረቶች በአግበቡ መያዛቸውን ማረጋገጥ

2.11 ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ስለማህበር ስራ አፈጻጸም ወቅታዊ ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎችን ማቅረብ

2.12 የማህበሩን ዓላማዎች ከግብ እንዲደርሱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን

2.13 አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ ካሉት ስልጣኖቹ መካከል በከፊል ለዋና ስራ አስፈጻሚው ወይም ለማንኛውም ለማህበሩ ስራ አመራር በውክልና መስጠት

አንቀጽ **11**

የማህበሩ ስራ አመራር

11.1 የማህበሩ ስራ የሚመራው በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሾም ዋና ስራ አስኪያጅ ነው።

11.2 ዋና ስራ አስኪያጁ በህግ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ማህበሩን የመምራት ኃላፊነት ይወጣል። ዋና ስራአስኪያጅ የማህበሩን ዓላማዎች እውን ለማድረግ አስፋላጊ የሆነ ተግባራን ሁሉ ያከናውናል።

አንቀጽ **12**

ኢዲተር

12.1 ማህበሩ በባላ አክሲዮን ጠቅላላ ጉባኤ የሚሾሙ እና የሚሻሩ በህግ የታወቁ ኦዲተሮች ይመርጣል። የኦዲተሩን ተግባራት እና ኃላፊነቶች በሚመለከት በኢትዮጵያ ህግ አንቀጽ 373-380 ባሉት ድንጋጌዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

12.2 የኦዲተሮች ክፍያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል።

12.3 በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚሾሙ ኦዲተሮች ለ 3(ሶስት) ዓመት ያገለግላሉ።

አንቀጽ **13**

ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው። ሆኖም ማህበሩ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንቀጽ 495 በተደነገጉት ድንጋጌዎች ወይም አግባብነት ባለው በማንኛውም ህግ መሰረት በማንኛውም ጊዜ ሊፈርስ ይችላል።

አንቀጽ 14

ሪፖርት ስለማውጣት

የማህበሩ ስራ እንቅስቀሴዎችንና የፋይናንስ አቋሙን ሚገልጽ አመታዊ ሪፖርት ለባለአክሲዮኖች ያሳውቃል።

አንቀጽ 15

ምዝገባ

ማህበሪ በሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ከተመዘገበ በኋላ የህግ ሰውነት የይኖረዋል።

መስራች አባላትም ከዚህ በታች በተያዘው የፊርማ ሰንጠረዥ በየስማቸው ፊትለፊት ፊርማቸውን በማኖር የማህበሩን ምስረታ አረጋግጠዋል።

ተ/ቁ	ስም ከነአያት	ፊርማ	መግለጫ